**ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል**

**23 ኛ ሳምንት**

**በደብረዘይት የተነገረው ምሳሌ**

**ዓላማ**

- የመንፈሳዊ ዝግጁነትን እምነትና መልካም ሥራን አስፈላጊነትና ጥቅም መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት"***

**መግቢያ**

- ምሳሌ ቀለል ተደርጎና መልእክት ለማስተላለፍ የሚቀርብ ምሳሌ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ምሳሌዎችን ለደቀመዛሙርቱ በደብረዘይት ነግሮቸዋል።
- በዛሬው ትምህርታችንም አንዱን እናያለን።ከነዚህ ምሳሌነት በኋላም ጌታችን ስለምጸአትና ስለፍረድ ቀን ነግሮቸዋል።
- በክብሩ ሲገለጥም በሕያዋንና በሙታን ይፈርዳል።

**ትምህርቱ**

- መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች።ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ አንቀላፉ /ተኙ/ እኩለ ሌሊትም ሲሆን፣ እነሆ ሙሽራው ይመጣል፣ ተቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ሁካታ ሆነ። በዚያን ጊዜም ቆነጃጅቱ ሁሉ ተነሱና መብራታቸውን አዘጋጁ።
- ሰነፎቹም ልባሞቹን፦ ***መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን*** አሉአቸው።
- ልባሞቹ ግን፦ ***ምናልባት ለእናንተና ለእኛ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ሄዳችሁ ግዙ*** አሉአቸው።
- ሊገዙ ቢሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፣ የተዘጋጁት ገቡ፣ ደጁም ተዘጋ።
- ሊገዙ የሄዱት ተመልሰው ***ክፈትልን*** አሉ።እርሱ ግን ***"እውነት እላችኋለሁ፣ አላውቃችሁም"*** አለ።
- ***ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።***

## ***ከዚህ ምሳሌ የሚከተለውን እንማራለን።***

**ዝግጁነት**

- ከአምስቱ ልባሞች ደናግል በመጨረሻው ሰዓት የምናገኘውን እድል እንዳናጣ መዘጋጀት እንዳለብን እንማራለን። ሰነፎቹ ከሙሽራው ጋር ያልገቡት ተጨማሪ ዘይት ይዘው ስላልተዘጋጁ ነበር።
- ይህ ምሳሌ ጌታችን በመግቢያው እንደነገረን የመንግሥተ ሰማያትም ምሳሌ ነው።
- ***ሙሽራው*** ክርስቶስ ነው።
- ***ልባሞቹደናግል***በቀድስና፣ሕገእግዚአብሔርንበመጠበቅና፣እርሱንበማምለክ፣ችግረኞችን፣ በመርዳትም የሚኖሩ ቅዱሳን ምሳሌ ናቸው።
- ***ሰነፎቹቆነጃጅት***ምየቀድስናኑሮየሌላቸውናለእግዚአብሔርመንግሥትራሳቸውን ያላዘጋጁ ናቸው።
- ***የሙሽራው መምጣትም*** የጌታ ደግሞ ምጽአት ነው።
- ***መብራቱ*** እምነት ***ዘይቱ*** የምግባራቸው ምሳሌ ነው።
- ከዚህናከአንድተጨማሪምሳሌበኋላም፤ጌታችንኢየሱስክርስቶስስለፍርድሲመጣምንእንደሚደረግለደቀመዝሙርቱ አስተምሮአቸዋል።
- ***"እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።....እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ ስንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።"***
- በግራው ያሉትንም ደግሞ ***"እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው ሂዱ።ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና... እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።"***
- ለሰነፎቹ ሴቶች እንዳላቸውም እነዚህንም ***"አላውቃችሁም"*** ብሏቸዋል።ከዚህ ጌታ ደግም ሲመጣ የሚክዳቸው አሉ ማለት ነው።
- ስለዚህ በእምነት ከመልካም ምግባርና ሥራ ጋር በመኖር የመንግሥቱ ወራሾች ለመሆን መዘጋጀት አለብን።ክርስቶስ "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ እንደሚለንና ሲፈጥረንም የመንግሥቱ ወራሾች ሊያደርገን እንደሆነም ያስረዳናል። በዚህ ካልኖርን ግን 'ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ የዘላለም እሳት' እንሄዳለን።

**ጥያቄዎች**

1 ስለ አሥሩ ደናግል የመሰለው ማነው?
2 ታሪኩን የት ነገራቸው?
3. ለሚቀጥለው ሳምንት ሁለተኛውን ምሳሌ አንብባችሁ ኑ?
4. የሙሽራው፣ የ10 ደናግል፣ የመብራቱና የዘይቱ ምሳሌዎች ምን ነበሩ?
5. ለመደበኛው ትምህርታችሁ ለፈተና የምትዘጋጁት እንዴት ነው? የፈተና ውጤታችሁ የዝግጅታችሁ ውጤት ነው?
6 ለመንፈሳዊ ሕይወታችሁ የምትጠቀሙበት መንገድና ዝግጅትስ? ከመምህር ጋር ተወያዩ።

**ይቆየን።**